# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

# Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ጳጉሜ 1 ቀን 2003 ዓ.ም

ለክቡር አቶ ሙስጠፋ አብደል ጀሊል
የሊቢያ የሽግግር ሸንጎ ሊቀመንበር
ቤንጋዚ/ትሪፖሊ
ሊቢያ

ክቡር ሆይ፤

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (በ1964 የተመሠረተና እስካሁንም አምባገነኖችን እየታገለ ያለው - ኢሕአፓ) ይህንን ደብዳቤ የሚያቀርበው በሊቢያ በሚገኙ የኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ እየተፈጸመ ያለውን አሳዛኝና አሰቃቂ ሁኔታ ክቡርነትዎ እንዲገነዘቡት ለማድረግ ነው። በጋዳፊ አገዛዝ ወቅት የኖሩበት ኢሰብዓዊ ሁኔታ (መደብደብ፣ መደፈር፣ በበረሃ ላይ በኮንቴይነር ታጭቀው እንዲኖሩ ማድረግ፣…ወዘተ) ያልበቃ ይመስል፤ አብዛኞዎቹ እነዚህ ስደተኞች (ጥቁር አፍሪካውያን ስደተኞችን ጨምሮ) በአማጽያኑም እየተሰቃዩ እንደሆነ ማወቅ ችለናል። ጥቁር መሆን ብቻ እንደማያወላዳ መረጃ ተወስዶ በርካታ ኢትዮጵያውያንና ሌሎች አፍሪካውያን ስደተኞችን እንደ የጋዳፊ ቅጥረኛ ወታደሮች (መርሰናሪዎች) አርጎ መውሰድ እጅግ በጣም የተሳሳተና ለበርካታዎቹ ሕይወት መጥፋትም ምክንያት ሁኗል። በዚህ የተነሳም በርካታዎቹ ስደተኞች በፍርሃትና በጭንቀት ተውጠው ከቤታቸው የማይወጡበት ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ከየቦታው እየተለቀሙ በእስር ላይ ይገኛሉ። የሚያሳዝነው ግን እነዚህ የስደተኛ እስረኞች፣ የጋዳፊ ወታደሮች ከሚገኙበት በባሰና አሰቃቂ የእስር ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙም መረዳት ችለናል። እናም የሊቢያ አረቦች በጥቁር አፍሪካውያን ላይ ዘረኛ አመለካከት አላቸው የሚለውን አባባልስ እንዴት አርጎ አሌ ማለት ይቻላል። ይህ ደግሞ አሁን በሊቢያ ለዴሞክራሲ መስፈን የሚደረገው ትግል ላይ የራሱ ጫና ሊኖረው እንደሚችል መገመት አያስቸግርም።

ክቡር ሆይ፤

ኢሕአፓ በእነዚህ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም በተቀሩት አፍሪካውያን ስደተኞችና ሠራተኞች ላይ ባጠቃላይ፣ የቆዳ ቀለማቸው ጥቁር በመሆኑ ብቻ (ከሲሶ በላይ የሚሆነው የሊቢያም ሕዝብ ያለው ማለት ነው) በአሰቃቂ ሁኔታ እየተፈጸመባቸው ያለውን በደል በይፋ እንዲያወግዙ ጥሪ ያደርግልዎታል። ኢሕአፓና ብዙ ዴሞክራሲያዊ አፍሪካውያን ለሊቢያ ሕዝብ ያላቸውን ድጋፍ ሲገልጹ መቆየታቸውም ይታወቃል። የሊቢያ የሽግግር ሸንጎና ታጋዮቹ ለኢትዮጵያውያን/አፍሪካውያን ሕይወት መከበር መቆም አሁኑኑ መጀመር አለባቸው እንላለን። ሊብያ ወገኖቻችንን ማሳደድ ሳይሆን ሕይወታቸው እንዲከበር ማድረግ ይኖርባታል። በሃኒባል ጋዳፊ የተጠበሰችው ወገናችን ፎቶ ነገ ያለምንም ትፋት በተገደሉ፣ ወይም በተደፈሩ ኢትዮጵያውያን/አፍሪካውያን ስደተኞች፣ ሠራተኞች ምስል መታጀብ አይኖርበትም እንላለን።

ለጉዳዩ ለሚሰጡት ግምትና ትኩረት በቅድሚያ እናመሰግናለን

EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com